የዕውቀት ብልጭታ

ከከበደ ሚካኤል

የዕውቀት ብልጭታ

ከከበደ ሚካኤል
ተጸፈ

አዲስ አበባ ፲፱፻፸፪ ዓ.ም.

“የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው!”

“All Right Reserved!”

ኢትዮጵያ ፤ አዲስ አበባ 2014 ዓ.ም.

መጀመሪያ ፲፱የካቲ ዓ.ም. ታተመ።

ሁለተኛ ዕትም 2014 ፪ጳጉሚ ዓ.ም.



ወገግታ አሳታሚ

WEGEGTA PUBLISHER

0911 51 94 37 / 0929 32 75 75

አሳታሚና አከፋፋይ ወገግታ አሳታሚ

+251-929-327-575

+251-911-519-437

መቅድም

ተርቦ ለመጣ ሰው ባዶ መሶብ ቢያቀርቡለት በውሥጡ እንጀራና ወጥ ካላገኘበት ሊጠግብ አይችልም። እናንተም በየትምህርት ቤቱ ያላችሁ ሕፃናት እንደዚሁ መጻሕፍት ከሌሉ የትምህርት ቤት ብቻ ቢከፈትላችሁ የትምህርቱን እንጀራ ልትመገቡ አትችሉም። ይህንንም ስላልሁ በትምህርት ቤት ውሥጥ በውጭ አገር ቋንቋ የተጻፉ በየዓይነቱ ትምህርት የምታገኙ ባቸው መጻሕፍት ተሰናድተው እንደሚቀርቡላችሁ አውቃለሁ። ግን ሕፃን የባዕድ ቋንቋ ተምሮ በውሥጡ ያለውን ምሥጢር ለመረዳት እስኪችል ድረስ ያለበት ድካም እኔም እንደ እናንተ ሕፃን በነበርሁ ጊዜ ስለደረሰብኝ ይህ ድካም እንዲቃለልላችሁ ባለኝ አቅሜ ሰረዳችሁ በጣም ደስ ይለኛል።

ታሪክና ምሳሌ ፫ኛ መጽሐፍ የተባለውን ከጻፍሑላችሁ በኋላ ደግሞ ይህን አስከትዬላችኋለሁ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የበለጠ ጥቅም እንድታገኙበት አስቤ ሁለት ዋኖች ነገሮች ተከትያለሁ።

አንደኛው በተረትና በጨዋታ አነጋገር ሆኖ የምታገኙት የሙቀትንና የብርድን የመጥፎ አየርንና የነፋስን ባሕርይ በአጭሩ የሚያስረዳችሁ ለጥበብ (ሲያንስ) ትምህርት መሰናጃ የሚሆናችሁ ንባብ ነው ይህንንም አብዛኛውን ያገኘሁት ቶል ስቶኢ ከሚባለው ከትልቁ የመስኮብ ደራሲ መጽሐፍ ውሥጥ ነው። እሱ ትልልቅ መጻሕፍት የጻፈ ዐዋቂ ሆኖ ሳለ ለሕፃናት የሚጠቅም ነገር ላሰናዳ ብሎ አሰቦ በመድከሙ በዓለም ላይ ያሉ በእሱ መጽሐፍ የሚማሩ ብዙ ሕፃናት አመሰግነውታልና እናንተም አመሰግኑት። ከእሱ ያገኘኋቸውን ሁሉ እመጨረሻው ላይ (ሌ ቶ) የሚል ምልክት አድርጌባቸዋለሁ ፤ ይህም ሌዎን ቶልስቶኢ ማለት ነው።

ሁለተኛውም በአለፉት መጻሕፍቶቼ የሚያጫውቱና የሚያስቁ ሆነው በውሥጣቸው ትምህርት ያለው ምሥጢር የሚገኝባቸው ተረቶች በግጥምና በስድ ንባብ እያደረግሁ አሰናድቼላችሁ ነበር። በዚህ በአሁኑ መጽሐፍ ውሥጥ ደግሞ ከፍ ካለ የትምህርት ደረጃ ስትደርሱ በዓለም ታሪክ ውሥጥ ከምታገኙዋቸው በየዘመኑ ተፈጥረው ከነበሩት ታላላቆች ሰዎች ጋር የሚያስተዋውቋችሁ ተረቶች ጽፌላችኋለሁ። በእነዚህም

ተረቶች ውስጥ ካምቢዝ ዲዎጋን ጀንጂስካን የሚባሉና እነሱንም የመሰሉ ሰዎች ታገኛላችሁ። ወደፊት በዓለም ታሪክ ላይ እንደምታገኙት እነዚህ ሰዎች በዓለም ላይ ትልልቅ ሥራ የሠሩ ስለሆኑ ካሁኑ ጀምሮ ስማቸውን ብታውቃቸውና ከባሕሪያቸውም ጥቂት ነገር ብታውቁ ይጠቅማችኋል።

በጣም ደግሞ አደራ የምላችሁ በብርሃነና መቅድም ውሥጥ ተናግሬው እንደነበረው የውጭ አገር ቋንቋ ከተማራችሁ በኋላ ስጦታችሁ በሚያደላበት ዕወቀት እየደከማችሁበት በውስጡ የምታገኙትን ፍሬ ነገር እያጣራችሁ ወደ አማርኛ ቋንቋ እንድትገለብጡትና ከናንተ በኋላ ለሚመጡት ልጆች አውርሳችሁ ቋንቋችሁን እንድታበለጥጉበት ነው።

የባዕድ ቋንቋ በወንዝ በምንጭ ወይም በጉድጓድ ውኃ መመሰሉን አትርሱ። ሰው ውኃ ወደ አለበት ስፍራ ሲሔድ በእንሥራ ወይም በመቅጃ አምጥቶ ለቤተሰቦቹ ካልሰጠ ለራሱ ብቻ ጠጥቶ ቢመለስ ድካሙ ፍሬ ሳይ ሰጥ መካን ሆኖ ይቀራል። የውጭ አገር ቋንቋ ተምሮ ብዙ መጻሕፍት ወደ አገሩ ቋንቋ የሚተረጉም ሰው ግን የወንዙን ውኃ በቦይ መልሶ ድርቀት የጎዳ ውን የአባቱን ርስት እያጠጣ በሚያለማ ሰው ይመሰላል። ከሌላው ቋንቋ ቀድተው ያመጡትን ለአገራቸው ቋንቋ ማሠልጠኛ ያደርጉታል እንጂ በሰው ቋንቋ ብቻ የሠለጠኑ ሕዝቦች አታገኙም። የውጭ አገር ቋንቋ ብቻ ውን ቢስፋፋ የሚጠቅም እንዳይመስላችሁ። ከባዕድ እየጐረስህ ወደ ዘመድህ ዋጥ የሚባለውን ተረት አስቡ።

ከዚህ ቀጥሎ በሚከተለው መቅድም እንደምትመለከቱት የእግዚአብሔር እርዳታ ተጨምሮ በንጉሠ ነገሥታችን ድካምና ብርታት ከጠፋች በኋላ የተገኘችው ነፃነታችን ዋጋዋ ከፍ ያለ መሆኑን እያሰባችሁ አገራችሁን በጣም ውደዱ፤ ለንጉሠ ነገሥታችሁም በቅንነት የመታዘዝ አሳብ በልባችሁ ይደር።

ደጉ ንጉሣችን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አገራቸው ኢትዮጵያ ከአዲሱ ሥልጣኔ ብዙ ነገር እንደሚገድላት ዐውቀው የሥልጣኔን ጎዳና የሚከፍቱ ብዙ ሥራዎች በሥራት ሲጀምሩ በጥባቦ እያለ ጥሩ ውኃ አይገኝም እንደሚባለው ኢትዮጵያ እንዳትሠለጥን የምትመቀኝ አጣለያ ተነሥታ ሥራቸውን አሰናከለችባቸው።

ከሥልጣኔ ደረጃ የደረሱ አገሮች ሁሉ እኛ ዛሬ በአለንበት አካሄን ውስጥ እነሱም እንደነበሩና የሥልጣኔ እርምጃቸውም የተፈጸመው በብዙ ድካምና በረጅም ጊዜ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል። ለምሳሌ የዓሥር ዓመት ልጅና የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ የሰውነታቸው ብርታት ትክክል ሊሆን አይችልም። እሱም በዚህ ዕድሜ ደካማ እንደነበረ ሳይገነዘብ የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ የሆነው የዓሥር ዓመቱን ልጅ ደካማ ነህ ብሎ ቢወቅሰውና ቢያጠቃው ያስነቅፈዋል እንጂ አያስመስግነውም።

አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ እንደሚባለው ተረት በመንፈሱ ከፉ አሳብ እየፀነሰ ኃይል አደራጅቶ ለማጥቃት የታጠቀ ግፈኛ በተነሣ ጊዜ ጉልበቱ የደከመ መስሎ የሚታየውን ጎረቤቱን ለመበደል ሲያስብ ጠብ ማንሻ የሚሆን ምክንያት አያጣም። ይህንንም የጀርመን ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ቢስማርክ "ኃይል ሕግን ይደመስሰዋል" ብሎ ተናግሮ ጨርሶታል።

ጀርመን በድብቅ የጦር ኃይል አደራጅቶ ከተነሣ በኋላ በሥልጣኔ ከራሳቸው ተርፈው ለሌሎች ያካፍሉ የነበሩትን አገሮች በጦር ጉልበት ይዞ በገንዘባቸውና በጉልበታቸው ላይ እያዘዘበትና ለጀሮ የሚቀፍ ልዩ ልዩ የግፍ ሥራ እየሠራባቸው በአገራቸው ውስጥ ተቀምጦ ገዝቷቸዋል። ይህንንም ለማድረግ የሚገባው መሆኑን ለማስረዳትና ለማሳመን አንድ ብቻ ሳይሆን ብዙ ምክንያት ይሰጣል። ቢስማርክ ኃይል ሕግን ይደመስሰዋል ያለው ይህ ነው።

እንዲሁም ደግሞ አትየጵያ በሰባት ወር ውስጥ ተሸንፋ ጣሊያኖች አዲስ አበባ መግባታቸው በኢትዮጵያውያን ዘንድ ቀድሞ ያገኝ የነበረው የጀግንነት መንፈስ እየቀዘቀዘ በመሔዱ መስለዋቸው የሚናገሩ ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ነበሩ በኋላ ግን የጦርነቱ እሳት በአውሮፓም ላይ ከነደደ በኋላ የአሌሮፕላንና የታንክ ኃያል የጦርነትን ሁኔታ በጣም እንደለወጠው ዓለም ተረዳው።

ፈረንሳዮችን የመሰለ በማናቸውም ረገድ የጐደለ ነገር የሌለውና ጀግንነቱም በዓለም ሙሉ የታወቀ ሕዝብ በአሥራ አምስት ቀን ሲፈታ ኢትዮጵያ በሌላ መሣሪያ በታንክና በአሌሮፕላን ስትወጋ ከዚህም የባሰ

ደግሞ በዓለም ሕግ የተከለከለ የመርዝ ጢስ ሲጣልባት ይህን ያህል ጊዜ ለመራከር መቻልዋ በጣም እንደሚያስመሰግናት አይጠረጠርም።

ይልቁንም ደግሞ ንጉሠ ነገሥቷ በጦር ሜዳ ላይ እንደ አንድ ተራ ወታደር ሆነው እስከ መጨረሻው ከተዋጉ በኋላ በአምስቱ ዓመታት የስደት ዘመን ውስጥ በአገራቸው አርበኞቻቸውን እያዋጉ ጠላት የሚሠራባቸውን የግፍና የፈተና ሥራ በትልቅ ትዕግሥት እየተቀበሉ በማይናወጥ የተከራካሪነት መንፈስ ታግለው የአገራቸውን ነፃነትና ሰንደቅ ዓላማዋን በማስመለሳቸው የተገኘው ክብር ታላቅ ነው። ይህም ክብር አሁን በዓይኖቻችን ከምናየው ይልቅ ወደፊት ለታሪክ የበለጠ መሆኑን አንዘንጋ።

ኢጣልያም በጠላትነት በአወራችውና እውነት እያስመሰለች በነዛችው ፕሮፓጋንዳ እየተታለሉ ኢትዮጵያ ጥፋተኛ ትመስላቸው የነበሩ ሕዝቦች ኢጣሊያና ጀርመን በዓለም ላይ ያመጡትን የጦር መዓት በኋላ ስላዩትና መከራውም ስለደረሰባቸው እውነተኛውን ነገር ገልጦ የሚያሳያቸው መልካም ማስረጃ ሆኖዋቸዋል።

በተአምሩ ረድቶ የአገራቸውን ነፃነት ለማስመለስና ክብርዋን ለማደስ እንዳበቃቸው ሁሉ እንዲሁም ደግሞ በትምህርትና በዕውቀት ኃይልዋን አጎልምሰው የሥልጣኔ ክብር ለመስጠት ያቀዱትን አሳብ ለመፈጸም እንዲችሉ የተወደዱ ንጉሠ ነገሥታችንን እግዚአብሔር በጥበቡ እንዲረዳቸው እንለምናለን።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከአምስቱ ዓመታት በኋላ ከስደት ተመልሰው በድል አድራጊነት ከመናገሻ ከተማቸው የገቡ ዕለት ለሕዝብ የታደለው ግጥም መታሰቢያ ሆኖ እንዲገኝ ከዚህ ቀጥዬ አግብቼዋለሁ።

ማውጫ

አርእስት	ገጽ
የዕውቶት ብልጣሁታ	3
የኢትዮጵያ ትንሣኤ	12
የተማረ ሰው ብልጫ	25
መልካም በተል	25
የውኃ ታሪክ	26
ሱልጣን ሞሐመድ	28
የወቅያኖስ ባሕር	28
ሀለት ሊቦች	29
ነፋስ	30
አንድ ትርንጎ	30
ዐሳይና ጨረቃ	31
አንድ ብልሀ ዓይነ ስዉር ሰው	32
ዲን ሱዊፍት	33
አንድ ገበሬና አንዲት ዐይጥ	35
ዲዎጋን	36
የገና ከንቱነት	39
የነፋስ ጠቃሚነት	41
ሦስት መንገደኞች	41

የጦር ሠራዊት ሥርዓት አፈጻጸም 42
ሙቀትና ቅዝቃዜ 43
አንድ ውለታ ቢስ ድኩላ 45
የኢታላይ ሰው ታማኝነት 47
ሻርልከ 51
አንድ ረጅም ሰውና አንድ አጭር ሰው 51
አትከልትና አረም 52
አንድ ጅል 53
ሽታና ውሻ 53
ጅንጂስካን 56
የውኃ ጉዞ 56
አቡንና ወንበዴ 57
አንድ ንጉሥና አንድ ሊቅ 60
ጅንኛስካንና ለማዳ አሞራ 60
መጥፎ አየር 64
አንድ መስፍንና አንድ ፈላስፋ 66
ካምዚዝና ፕሳሜኒት 75
ከሕግ የወጣ ትርፍ 77
ሁሉም የሆነ ነው 78
አባትና ልጅ 81

የቀኝ አገር ወርቅ የሰላም ጠንቅ 82
ትንቢተ ዮናስ 92
ከመጠጥ የሚመጣ ጉዳት 99
የአንድ ሰካራም ታሪክ 102
መታዘዝን ዕወቅ 104
የካምቢዝ ጭካኔ 107
ብልህ ራሱን ያድናል 109
አንድ አዳኝ ሰውና አንዲት ዋኔ 111
አንድ ሰው አንድ አንበሳና አንድ ድብ 113
አንድ ዚቀኛ 115
በማር ጠብታ አገር ተመታ 115
የገንዘብ ፍቅር 118
ዓሣ አጥማጅና ዛጎል 119
ስለ ተግባረ እድ 121
አግኝቶ ያጣ ሰው 126
ጥቅሮችም እንደ ሰው 128
የበረሃ መንገደኛ 130
የአዚናራ እስረኛ 131
የፀሓይ ባሕሪ 136
የልቦና ሥልጣኔ 137

የመሬት ሁኔታ 140
የሐር ትል 142
ዛሬና ነገ 142
ሲ ሊንግ ሺ የምትባለው የቺና አገር ንግሥት 145
ሙዚቃ 146
የሥራ ጥቅም 148
ስለ ጨረቃ 149
የሐር ትል በቡከሐራ አገር እንደምን እንደገባ 150
ኮከቦች ፕላኔቶችና ጅራታም ኮከቦች 151
ዬ ኪያንግ 155
ቡሶል 156
ዕብነ አድማስ 157
ካሎሪክ 157
ቴርሞሜትር 158
ሺሚ 158
አዬ ቴዎድሮስ 160
ንጹሕ አካሎችና ቅልቅል አካሎች 164
የውኃ ሁኔታ 164
የአየር ባሕሪ 165
አቶም 165

አኒባል 169
አስትሮኖሚ 174
ያስብ ጥልቅ አስተያየቶች 179



ከበደ ሚካኤል በኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ገናና ከሆኑት ደራሲያን አንዱ ናቸው። ጥቅምት 23 ቀን 1909 ዓ.ም. የተወለዱት ባለቅኔ የቤተክህነትን ትምህርት ካገባደዱ በኋላ በአሊያንስ ፍራንሲዝና በሳዛሪስት ሚሲዮን ዘመናዊ ትምህርትን ተከታትለዋል። የግሪክ፣ የሮማውያን፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የጀርመን፣ የሩስያና የጣሊያንን በርካታ መጻሕፍት ከመረመሩም በኋላ ሃያ ስድስት መጻሕፍትን ለወገኖቻቸው አበርክተዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለዚሁ ተግባራቸው የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በ1990 ዓ.ም በሰጠበት ወቅትም፤ "በድርሰቶቻቸው ውስጥ የሚታዩት የእኒህ ታላቅ ደራሲ የሐሳብ መግለጫዎች፣ ቃላት፣ ዘይቤዎች እና ሌሎች የአጻጻፍ ስልት ገፅታዎች በኋላ ለመጡ ደራሲዎች ያደረጉት አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም። በተለይ ከ1950ዎቹ ወዲህ የተነሱ በርካታ ደራሲዎች የእሳቸውን ድርሰቶች አንብበው፣ በሳቸው ድርሰቶች ሥነ ጽሁፍን አውቀውና አጣጥመው ደራሲ ሊሆኑ በቅተዋል" ብሏል።

ወገግታ አሳታሚ እና የጎትመት ሥራዎች የኒህን ሊቅ ሥራዎች ጠቃሚነት በማጤንና ለዘመናችን ትውልድ የሚኖራቸውን ፋይዳ በማሰብ እነዚህን መጽሐፎቻቸውን ለአንባቢያን አቅርቧል።

ደራሲው ከዚህ ቀደም ካሳተሟቸው ሥራዎች መካከል።

- ብርሃነ ሕሊና
- መጀመሪያ እርምጃ
- ታሪክና ምሳሌ 1ኛ መጽሐፍ
- ታሪክና ምሳሌ 2ኛ መጽሐፍ
- የትንቢት ቀጠሮ (ቴአትር)
- የቅጣት ማዕበል "
- ሮሜዎና ዠልየት "
- አኒባል "
- የቅኔ ውበት
- የአለም ታሪክ
- ጃፓን እንደምን ሠለጠነች?
- ኢትዮጵያና ምዕራባዊ ሥልጣኔ
- ከይቅርታ በላይ
- ትልቁ እስክንድር (የሕይወቱ ዜና)
- ታላላቅ ሰዎች

ወገግታ አሳታሚ
WEGEGTA PUBLISHER
0911 51 94 37 / 0929 32 75 75

ዋጋ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር

ዋጋ ብር 250